# ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞ ቅጽ 41 ቁ 1 መስከረም 2008 ዓ.ም.


## አሮጌው 2007 ዓ.ም ተገባዶ አዲሱ ሲተካ!

## የት ላይ ነን? ምንስ ይጠብቀናል?

በሀገራችን የዘመን አቆጣጠር መሠረት ሕዝባችን 2007 ዓ.ም ዘመነ ሉቃስን አሳልፎ ወደ አዲሱ 2008 ዓ.ም ዘመነ ዮሃንስ ከተሸጋገረ ጥቂት ቀኖችን አሳልፏል። የሰው ፍጡር በህይወት እስከኖረ ድረስ ማንኛውም ዜጋ እንደ አቅሙና ችሎታው፤ መድረስ ከሚፈልገው ሁለንተናዊ የኑሮ መሻሻል አንፃር ባለፈው ዓመት በክፉም ሆነ በደጉ የተጓዘባቸውን ሂደቶች፣ በቀን ተቀን ሕይወቱ ያጋጠሙትን ችግሮች በሕሊናው እያሰላሰለና እየመረመረ ለመጪው ወራት ለራሱም ሆነ ለቤተሰቡ እንዲሁም ከፍ ሲል ለሀገሩና ለወገኖቹ መልካም ምኞቱን መግለጽ ብቻ ሳይሆን ምን ማድረግ እንዳለበትም እቅዱን እያለመ አዲሱን ዓመት በተቻለው መጠን እንዳመጣጡ ለመቀበል መንቀሳቀሱ የሚጠበቅ ነው።

በመሆኑም አሮጌው ዓመት በአዲሱ ሲተካ የሀገራችንን አጠቃላይ ሁኔታ በተለይም ያለፈውን ዓመት በጥልቀት መዳሰሱና ጠቃሚ ግንዛቤን መጨበጥ፤ የምንጓዝበትን የወደፊት አቅጣጫና መድረስ ከምንፈልገው ሁኔታ በፖለቲካ መነፅር አማትሮ ለማየት የሚረዳ እንደሆነ ግልፅ ነው። ይህም በትግል ላይ ለሚገኝ ማንኛውም ግለሰብ ዜጋም ሆነ የፖለቲካ ድርጅት በሂደት የተደረጉ ስህተቶችን ላለመድገም የሚረዳ ብቻ ሳይሆን በትግሉ ሂደት የተደረሰበትንና በወቅቱ የምንገኝበትን ሁናቴ በማጤን ትግላችን ስኬታማ ይሆን ዘንድ ምን ማድረግ እንደሚጠበቅብን ለመተለም ፍቱን ማሳሪያ እንደሆነም ከተመክሮ የምንገነዘበው ነው።

ሕዝባችን እጅግ በተወሳሰቡ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ተተብትቦ ተይዟል። በድኽነት፣ በበሽታ፣ በመብት እጦትና በአስተዳደር ጉድለት፣ በአጠቃላይ በማኅበራዊ፣ ኤኮኖሚያዊና የፖለቲካ ችግሮች ምክንያት ክፉኛ እየተጠበሰ ይገኛል። ኢሕአፓ በመብት አልባነት እየተሰቃዩ የሚገኙትና በእስር እየማቀቁ ያሉት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎቻችንና የቅርብ ቤተሰቦቻቸው በመጭው ዓመት ጽናቱን አግኝተው እንዲጠናከሩ ፤ ጤንነት የጎደላቸው ፈውስን እንዲያገኙ፤ በድህነት አረንቋ የሚሰቃዩት ከችግራቸው እንዲላቀቁ፤ መልካም አስተዳደርና ፍትህ እንደሰማይ እርቋቸው እሮሮ የሚያሰሙት ሰሚ እንዲያገኙ መልካም ምኞቱን እየገለፀ፤ በአዲሱ ዓመት ለነፃነታቸውና ለዴሞክራሲ መብቶቻቸው መከበር የሚያደርጉት ትግል ስኬታማ ይሆን ዘንድ ልባዊ ምኞቱን ይገልፃል።

መልካም ምኞት ከመግለጽ ባሻገር መነገር ያለበት እውነታ ግን፣ አሮጌው በአዲሱ ዓመት መተካት ለውጥ የሚያመጣ ቢሆን ኖሮ በእርግጥም ባለፉት 40 ዓመታት ውስጥ ሕዝባችን የሚገኝበት ሁናቴ ካሁኑ በጣም የተለየ በሆነ ነበር። ሕዝባችን የተፈጥሮ ፀጋ የሆነውን የነፃነት መብቱን ስላልተጎናፀፈ፤ የተጫነበትን ቀንበር ከትከሻው አሽቀንጥሮ ለመጣልና የወያኔን አገዛዝ ለአንዴና ለሁሌም አስወግዶ መብቱን ለመጎናጸፍ ለበርካታ ዓመታት ጥረት አድርጓል፤ ታግሏል፤ ቁርጠኝነቱንም በተደጋጋሚ መስዋዕትነትን በመክፈል አሳይቷል። ይሁን እንጅ ቀኖች በሳምንታት፤ ሳምንታት በወራት፤ ወራት በዓመታት እየተተኩ ቢሄዱም ለሕዝብ ቀናኢና ሀገር ወዳድ የሆነው ኃይል ተባብሮና ጠንክሮ ባለመገኘቱ በተከታታይ ያለመታከት ያደረጋቸው ጥረቶቹ፣ ትግሎቹ፣ ድካሙና መስዋዕትነቱ ለጠላቶቹ የሥልጣን መቆናጠጫ እየተደረጉ እስካሁን ድረስ የድሉን ፍሬ ሊቋደስ አልቻለም።

የሩቁን ትተን በኢሕአፓ የሕይወት ዘመን እንኳ በነበሩ ሶስት አገዛዞች ሥር የነበረውን ሁኔታ ስናጤን ሕዝባችን ሰላም የሰፈነበት፤ የዜጎች እኩልነትና መልካም አስተዳደር የሚከበርበት፤ ባጠቃላይ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ዋስትና የሚያገኙበት ሥርዓት ለማስፈንና እንዲሁም የራሱን እድል በራሱ ለመወሰን የሚችልበት መድረክ ለማግኘት ያደረገው እልህ አስጨራሽ ተጋድሎ ገና ስኬታማ ባለመሆኑ፤ የጭንቀቱ ቀኖች እየተራዘሙበት፤ የትግሉን ፍሬ እየተነጠቀ ሁሌም መስዋዕት እንዲከፍል እየተደረገ ሲሆን ለነዚህ ችግሮች ለተዳረገ ሕዝብ የምኞት ተስፋ ማዥጎድጎድ ብቻዉን ትግሉን ዳር እንደማያደርሰዉ ለሱም ሆነ ለኛ ግልጽ ነዉ። በመሆኑም በአዲሱ ዘመን የሚያነሆልሉና ቃናቸው ጣፋጭ በሆኑ ቃላቶች የተዋቡ የምኞት መልክቶችን ማስተላለፍ ብቻ ሕዝባችን ከኛ የሚጠብቀው አይደለም ብንል ከውነቱ የራቀ አነጋገር አይሆንም። ይልቁንስ አግባብ የሚሆነውና እንደ ሕዝብና እንደ ሀገር በርካታ ተመክሮዎችን ያካበተው ሕዝባችን ከኛ የሚጠብቀው ቁም ነገር አሁንም ድረስ በጫንቃው ላይ ተቆናጦ ያለውን ጎጠኛና አምባገነናዊ ሥርዓት ከሥር መሠረቱ ደምስሶ ለመጣልና በምትኩ የራሱ፣ በራሱና ለራሱ የሚመጥነውን ነፃነቱን ተጎናፅፎ፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት ይችል ዘንድ ድክመቱን ለማስወገድ፤ የላላዉን አንድነቱን እንደ ብረት አጠንክሮ ቆራጥ ትግሉን እስከመጨረሻው ለመቀጠል የሚያስችለውን አቅጣጫ እንድንጠቁመው፤ ዜዴውን እንድናሳየውና ተግባራዊ እንድናደርገው መሆኑን በሚገባ እንገነዘብለታለን።

በርግጥም ለበርካታ ዓመታት በተለይም ደግሞ ባለፉት 42 ዓመታት በዓይነትና መልክ የተለያዩ ነገር ግን በሕዝብ በዳይነታቸውና ጨቋኝነታቸው ተመሳሳይ የሆኑ አገዛዞች ተፈራርቀውበት ህይወቱን ምስቅልቅሉን በማውጣት ለተለያዩ አሳዛኝና አሰቃቂ እንግልቶች ዳርገውታል። አሁን በሥልጣን ላይ ያለው የወያኔ አገዛዝ ካለፉት የተለየ የሚያደርገው መሠረታዊ ነጥብ ሕዝባችን በህይወቱ ምንጊዜም አስቦት በማያውቀው በዘረኝነት የተቃኘ ሥርዓት በጫንቃው ላይ አስፍሮበት፤ በመካከሉ ያለውን አንድነቱን እየሸረሸረበት፤ ሀገሩን እንደሀገሩ ለማቆየት እንዳይችል መጠነ ሰፊ የሆኑ ከፋፋይ ሴራዎችን እየጎነጎነበት የሚገኝ በመሆኑ ነው። በዚህም አገዛዙ የኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜትና በተለይም ደግሞ የኅብረ ብሔር ጠላት መሆኑን በራሱ ድርጊት እያስመሰከረ መገኘቱም ትግሉን ይበልጥ ውስብስብ እያደረገበት መገኘቱ ነው።

ይህ ብቻ አይደለም። ከአንድ አናሳ ብሔር የተውጣጡ መሰሪ ጎጠኞች የተሰባሰቡበት የአንድ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭነት በጫንቃው ላይ ተጭኖ ብሔራዊ ወንጀል እየተፈፀመበት ይገኛል። መሠረታዊ የሆኑ የሥርአቱ ተቋማትና ተግባራት በዚሁ ጎጠኛና አምባገነን ቡድን አባላት በብቸኝነት የተያዙ ናቸው። ከፍተኛውን የሥልጣን እርከን ጨምድደው ከያዙት ጥቂት ምርጦች አንስቶ በተለያዩ የአገዛዙ ተቋማት እንደ መከላከያ፣ የጦርና የፖሊስ፣ የፀጥታና የደህንነት፣ የምክር ቤትና የዳኝነት ክፍሉ በዚሁ ቡድን ከፍተኛ ባለሥልጣናት ሙሉ ቁጥጥር ሥር ናቸው። የሀገሪቱ ጠቅላላ የኤኮኖሚ ተቋማት፤ የመገበያያ እንቅስቃሴዎች፣ የገንዘብና የፋይናንስ ተቋማት፤ ከችርቻሮ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የንግድ አስመጪና ላኪ እንዲሁም በርካታ የንግድ ሱቆች ሁሉ በአገዛዙ ከፍተኛ ባለሥልጣናትና ጥቂት ደጋፊዎቻቸው የተያዙ ናቸው። ከሕዝብ እየዘረፉ የሚያግበሰብሱትን ሀብት ወደ ባዕዳን ሀገር ለማሸሽ የሚያስችላቸው የተለያዩ የባንክ ተቋማት በመመስረትና በራሳቸው ቁጥጥር ሥር በማዋል እየተገለገሉ ይገኛሉ። ከግሎባል ፋይናንሺያል ኢንተግሪቲ አንስቶ በተለያዩ የዜና ተቋማት እንደተገለፀው በሕገወጥ መንገድ ከሀገር የወጣው የገንዘብ ልክ አንዴ 11 ሌላ ጊዜ ደግሞ 14 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ መሆኑ የሚያረጋግጠውም ይህንኑ የዘረፋ መረብ ነው። በስርቆትና በዝርፊያ በመታገዝ የተገኘ የሕዝብን ሀብት ሕገ ወጥ በሆነ ሁኔታ ወደ ባዕዳን ባንክ ማሸሽ የሚያስከትለው ደግሞ ለተለያዩ መሠረተ ልማት ግንባታ ሊውል የሚችል የካፒታል እጥረት፤ የሚሰበሰብ ቀረጥ መቀነስ፤ በዜጎች መካከል የሃብት ልዩነት መስፋፋት፤ ጤናማ ውድድርና የንግድ እንቅስቃሴን ማምከን፤ የውጭ ምንዛሬ እጥረት መከሰትን ማስከተሉ ነው። ይህ ሁናቴ በአፍሪካ አንጎላ፤ ካሜሮን፤ ሱዳን፤ ታንዛኒያ፤ ኢትዮጵያ ጋቦን፤ ማዳጋስካር፤ ሞዛምቢክ፤ ናይጄሪያ፤ ዛምቢያ፤ ደቡብ አፍሪካ፤ ታንዛኒያና ዚምቡዋቤ የተከሰተና ከፍተኛ ጉዳትም ያደረሰ ነው።

የትምህርት ሥርዓቱንም ብንመለከት ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንዳትቀጥል የተጎነጎነ የወደፊት ሀገር ተረካቢ የሆነው ትውልድ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ስሜት እንዳያድግ ተብሎ የተቀመረው ሥርዓት በዚሁ የጎጠኞች ቡድን ነው። ባሰቡት ደረጃ ባይሆንም ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ በብሔረሰብና በሃይማኖት እንዲለያይ መደረጉ የዚሁ ፖሊሲያቸው ውጤት ነው። ትላልቆቹ ብቻ ሳይሆኑ በሁሉም የእምነት ተቋማት የራሱን ካድሬ ጳጳሳትና ሃጂዎችን ሰርጎ በማስገባትና በራሱ ቁጥጥር ሥር በማዋል፤ ምዕመናን በሃይማኖታቸው ቀኖና መሰረት በሰላም ፈጣሪያቸውን እንዳያመልኩ እያሴረ ለአገዛዙ መጠቀሚያ አድርጓል። የጋራ ሀገራቸውን በአንድነት እንዳይከላከሉ የከፋፋይ ሴራ ዘርግቶባቸዋል። የዜናና የሕዝብ መገናኛ ተቋማት በአገዛዙ ልማታዊ ጋዜጠኛ ተብዬዎች ሙሉ ቁጥጥር በመሆናቸው የሕዝብን ፍላጎትና አስተያየት ማንሸርሸሪያ ሳይሆኑ የአገዛዙ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ማስተጋቢያ ናቸው። የማንነቱ መገለጫ የሆነችው የሀገሪቷ ታሪካዊ ሰንደቅ አላማ በአደባባይ እንዳትውለበለብ በሕግ ተከልክላለች።

የሀገሪቱ የመጓጓዣና መገናኛ፣ የህንፃና የመንገድ ሥራ ሁሉ ሳይቀር ከአገዛዙ አባላትና ደጋፊዎች ውጭ የሚታሰቡ አይደለም። በተለያዩ ዘዴዎች ከነዚሁ ተቋማት ተመንጥረው በተባረሩ ዜጎች ምትክ በአገዛዙ አባላትና ደጋፊዎች እንዲያዙ ተደርገዋል። ይህ ቡድን ከባንክ እንዳሻው "ብድር" የመውሰድ ሥልጣን ሲኖረው ሌላው ከነሱ ውጭ ያለው የብድር ተጠቃሚ የመሆን እድሉ በጣም የጠበበና እጅግ የመነመነ ነው። ከፍተኛ ትርፍ በሚያስገኙ የኤኮኖሚ ዘርፎች ውስጥ ዋና ተዋናይ የሆኑት እነዚሁ ጠባብና ጎጠኛ ቡድን አባላትና ጥቂት ደጋፊዎቻቸው ናቸው። የከተማና የገጠር መሬት የአገዛዙ ንብረትና በነሱ ሙሉ ቁጥጥር ሥር በመደረጉም ገበሬውና አርሶ አደሩ ለነሱ ጭሰኝነትና ቁጥጥር መዳረጋቸው ብቻ ሳይሆን ያለ ሕዝብ ፍላጎትና ፍቃድ ለም የሆኑ መሬቶች ለባዕዳን በርካሽ ዋጋ እየተቸበቸቡ ገበሬዎች እንዲፈናቀሉ በማድረግ ለድህነትና ጉስቁልና ተዳርገዋል። የግጦሽ መሬታቸውን ተነጥቀዋል። ከአገዛዙ በመለጠፍ የጥቂቶች ባለ ሚሊዮን ሃብታም መሆን ይህንን ሐቅ ሊቀይረው አይችልም። የከተማ መሬትንም በሚመለከት ለሙስና እጅጉኑ የተጋለጠ በመሆኑ በየጊዜው በሕዝቡ እየተነገረ ያለው አቤቱታና እሮሮ የሚያረጋግጠው ነው። ተገነቡ የሚባሉት ትላልቅ ግንቦችና የመኖሪያ ቤቶች በማን ባለቤትነት ሥር እንዳሉ የአደባባይ ሚስጢር ነው። በከተማም በልዩ ልዩ ምክንያት ከተወለዱበትና ካደጉበት ቤት እየተነቀሉ የትም ተጥለዋል። ቀደም ብሎ በአጭር ጊዜ ውስጥ ባለሚሊዮን ሃብታም የነበሩት ዛሬ ዛሬ ባለእልፍ ሚሊዮነኞች (በቢሊየነሮች) ተተክተዋል። ። በአጭር ጊዜ ውስጥ ቁጥራቸው በውል ያልታወቁ ቢሊየነሮች መኖራቸው ከመነገሩ ሌላ ያከማቹት ሀብት በሀገር ወስጥ ባቻ ሳይሆን በውጭ አገር በልዩ ልዩ ዘዴና በተለያዩ ስሞች ተመዝግበው መገኘታቸው የአደባባይ ሚስጢር ከሆነ በርካታ ጊዜያቶች አልፈዋል። ለዚህም ነው ኤኮኖሚው ባለ ሁለት አኃዝ እድገት አሳይቷል በተባለበት ሁኔታ የተገኘው ሀብት ሁሉም እንደ አቅሙና ችሎታው ለመቋደስ ካልቻለ ብዙኀኑ የበይ ተመልካች የሚሆንበት ምህዳር እንደሚከሰት ተደጋግሞ እየተገለፀ ያለው። በርግጥም በሀገራችን የሚታየው ይኸው እንደሆነ ማንም ሊክደው የሚችለው አይደለም።

በአሁኑ ወቅት ሀገራችን የወያኔን አገዛዝ አቅፈውና ደግፈው በሥልጣን ለማቆየት ከፍተኛ ጥረት ከሚያደርጉት ሀገሮች የበለጠ ረጅም ታሪክ፣ አኩሪ ባህልና ቅርስ፣ ነባር እምነትና ግብረገባዊ እሴቶች ያላት አገር መሆኗ እያታወቀ፣ ማንነቷ ሆን ተብሎ እየተንቋሸሸ የአገሪቷ ወጣት ሴቶች ክብረነክ በሆኑ ተግባራት እንዲሰማሩ ተጽእኖ እየተደረገባቸውና ለዘመናዊ ባርነት በአገዛዙ አሻሻጪነት ወደ ባዕድ ሀገር እንዲጓዙ እየተደረገ ነው። በሚደርስባቸው በደል ምክንያትና ብሩህ ተስፋን በማጣት ለስደት የተዳረጉት፤ በመንገድ ላይ ውድ ሕይወታቸውን ከመክፈል ጀምሮ የተለያዩ የውስጥ አካላቸው ክፍል በወንበዴዎች ተቀዶ እየወጣ የተሰቃዩ ወጣት ኢትዮጵያዊያን ቁጥር በርካታ ነው። ጭንቁ በዚህ ብቻ አላበቃም። የወያኔ አገዛዝ ለመቀበል ያንገራገረበትና እና ለመካድ ዳድቶት የነበረው አሰቃቂ ሁኔታ በሊቢያ 28 ኢትዮጵያውያን በግፍ መታረድ ነው። ሌሎችም በጥይትም ተደብድበዋል። አሁንም በሊቢያ የማጎሪያ ቤቶች የሚሰቃዩት ብዙ ናቸው። በደቡብ አፍሪካም ሰላማዊ የሆኑ ወገኖቻችን በሚያሰቅቅ ሁናቴ በግፍ ተገድለዋል፤ በእሳት እንዲጋዩ ተደርገዋል። በሳውዲ አረቢያም ሆነ በሌላ አረብ ሀገራት ራሳቸውን የገደሉ፤ በአሰሪዎቻቸው ለተለያዩ አሰቃቂ በደሎች የተዳረጉ በርካታዎች ናቸው። በሊቢያ ያሉ የዜጎቻችን ዋይታ፣ በየመን የድረሱልን ጥሪና አገር ጥለው የወጡና ዛሬም መሔጃ አጥተው በጭንቅ ላይ ያሉ እንዲሁም በሜድትራኒያንና በቀይ ባሕር ሰላጤ ከባሕር የሰመጡት ወጣቶች በርካቶች ናቸው:: ለዚህ ሁሉ ተጠያቂ አረመኔው የወያኔ አገዛዝ ብቻ ነው።

ተደጋግሞ እንደተገለፀውና በተጨባጭም እንደሚታየው ሕዝባችን ላለፉት 42 ዓመታት የታገለላቸው ጥያቄዎችና ፍላጎቶቹ ሊሟሉ ቀርቶ በቀላሉ ሊወገዱ የሚችሉ ሁኔታ ካለመኖሩ በላይ እንከኖች እየተደራረቡበት በከፍተኛ ስቃይና በደል ውስጥ ለመኖር መገደዱ ቀጣይ መገለጫው ሆኖ ይገኛል። ለችግሮቹ መፍትሄ ለመስጠት የግዴታ በአዲሱ ዓመትም ፀንቶ፣ ቆርጦ መታገልና መስዋዕት መክፈል ግዴታ መሆኑ ደግሞ እንደ ጥላ የሚከተለው የመከራ እጣው ሆኖበት ይገኛል። የዛሬ 24 ዓመት በጠመንጃ በባእዳን እርዳታ ሥልጣን የያዘው የወያኔ ቡድን አሁንም ሥልጣኑን በነፍጥ ቁጥጥሩ ስር አድርጎ ይገኛል። በእነዚህ ዓመታት ሥልጣኑን የበለጠ ለማደላደል፣ ፖለቲካዊ ቅኝት ባለው የሕግ ማዕቀፎችና ሂደቶች እንዲሁም በባዕዳን ድጋፍ ጭምር እየታገዘ ሀገር ወዳድና ለሕዝብ ቀናኢ የሆኑ ተቀናቃኞቹን ለሞት፣ ለስደት፣ ለእስርና ለተለያዩ እንግልቶች እየዳረገ የቀጠለ ሲሆን እየደረሰበት ያለውን ተቃውሞ ሊያጠፋ ቀርቶ ሊያለዝብ እንኳን የሚቻለው አልሆነም። እንዲሁም የራሱንም የአምባገነንነት አገዛዝና ፈላጭ ቆራጭነት ለአፍታም ቢሆን የሚያደበዝዝበት መድረክ ሊፈጥር የሚችል አይደለም። በተከታታይ ያካሄዳቸው ምርጫ ተብዬ እንቅስቃሴዎች ሥልጣንን በቁጥጥር በማድረግ የተቃኙ በመሆናቸው ይህንኑ የሚመሰክሩበትና የበለጠ የሚያጋልጡት ናቸው።

ይህንን የወያኔ ጎጠኛ የሆነ አገዛዝን አቅፈው ደግፈው ለሥልጣን ባበቁትና አሁንም ድረስ መጠነ ሰፊ እርዳታ በሚለግሱት የምዕራብ ኃያላን መንግሥታት ዘመናዊና ዴሞክራት ተብሎ ቢሞካሽም ለሕዝባችን የተረፈው ነፃነቱን መጎናፀፍ፤ ሰላምን ማግኘት፤ መብቱ ተከብሮለትና መልካም አስተዳደር ተመስርቶለት በእድገት ጎዳና መጓዝ ሳይሆን ብሔራዊ ውርደትን በመከናነብ ለተለያዩ በደሎችና ጭቆናዎች መዳረግና ሰለባ መሆንን ነው። ይህ የነሱን ሙገሳና እርዳታን ተመርኩዞ

የተመሠረተው ሥርዓት የባዕዳንን ብሔራዊ አጀንዳ ለማስፈፀም የተፈጠመ ነውና የተለያዩ ቀለማት እየቀቡ ሊያቆነጃጁት ቢጥሩም አምባገነናዊ ከመሆን አላመለጠም። እንዲያውም የዛሬ 24 ዓመት የተዘረጋው የአንድ ቡድን አምባገነን አገዛዝ በነሱ መጠነ ሰፊ የፖለቲካና የኤኮኖሚ እርዳታ ተስፋፍቶና ተጠናክሮ ተገኘ እንጂ የዴሞክራሲ ካባ ሊላበስ ጨርሶ አልተቻለውም። በመልካም አስተዳደር እጦት፤ እጅጉኑ ሥር በሰደደ ሙስናና የፀረ ዴሞክራሲ ተግባራት ምክንያት ሕዝቡ እየደረሰበት ያለው ፈተናና ችግር በአሳዛኝነቱና በአሰቃቂነቱ ወደር የማይገኝለት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ዛሬም የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መታፈናቸው ቀጣይ ሆኖ ይገኛል። መብታቸው ተገፎና ነፃነታቸው ተዳፍኖ በአምባገነን አገዛዝ ለመኖር አሻፈረን ያሉ ከ 40 ሺ በላይ የሚሆኑ ዜጎቻችን በተለያዩ የማጎሪያ ቦታዎች ታጉረው የተለያዩ ስየሎች እየተፈፀመባቸው ይገኛሉ። በሺዎች የሚቆጠሩ በአገዛዙ ታፍነው የደረሱበት ጠፍቷል። የፕሬስ ነፃነት ተዳምጠዋል። ከባዕዳን የተኮረጁና በአለም አቀፍ ሰላም ወዳድ ኃይሎች ተቀባይነት ያላቸውና በመልካምነት የሚታዩ የሕግ አንቀፆችን "ሀሳብን በነፃ የመግለጽ፤ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ፈጥሮ በግምባር ቀደምትነት የመንቀሳቀስ፤ በሰላማዊ ሰልፍና መሰል እንቅስቃሴዎች የወያኔን አገዛዝ የማውገዝ፤ ተቃውሞ የማሰማት መብቶች" የመሰሉ በአገዛዙ የፖሊቲካ ፕሮግራም በሆነው ሕገ መንግሥት ተብየው ሰነድ ውስጥ አካቶ መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ቢነዛም እነዚህ አንቀፆች በተግባር ሲፈተሹ ግን በሽብርተኛነት የሚያስከስሱና በአነስተኛው ለብዙ ዓመታት እስራት ፍርድ የሚያሰጡ መሆናቸው የሕዝባችንን የቀን ተቀን የሰቆቃ ኑሮ ሁናቴ ገላጭ ኩነቶች ናቸው። በቅርቡ እንኳ የወያኔው ፍርድ ቤት በሰጠው ትእዛዝ መሠረት በነጻ ከእስር እንዲለቀቁ የተወሰነላቸው የተቃዋሚ ድርጅቶች አመራሮች እንደገና በእስር እንዲቆዩ መዳረጋቸው፤ የበላዩ ሕግ ሳይሆን የባለሥልጣናት ቀጪን ትዕዛዝ መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ብቻ አይደለም። የወያኔ የፌደራሉ አቃቤ ሕግ ሽብርተኛ ከተባለ ድርጅት ጋር ግንኙነት ፈጥረዋል፣ በማኅበራዊ ድረ-ገጾች ላይ መረጃ ማሰራጨትና ከሽብርተኛ ድርጅቶች ገንዘብ እንደሚላካላቸው ተደርሶባቸዋል በማለት ታስረው እንዲሰቃዩ ካደረጋቸው 10 የፓርቲ አመራሮችና ሌሎች መካከል በወያኔ ትእዛዝ ነሐሴ 14 ቀን 2007 ዓ.ም. አምስቱ ከእስር እንዲለቀቁ ቢወሰንም በሌላ የወያኔ ቡድን ውሳኔው በተግባር ሳይውል መቅረቱ የሕግ ልዕልና ጨርሶ የሌለ መሆኑን አመልካች እንጂ ሌላ አይደለም። እነዚህ ለአብነት ተጠቀሱ እንጂ ከከተማው ወጣ ብሎ በተለይም በገጠሩ በጠገቡ ካድሬዎች ተመሳሳይ እርምጃ የሚወሰድባቸው ዜጎች በርካታዎች ናቸው። ባጠቃላይ በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ የሕዝቡ የቀን ተቀን ኑሮና የአገሪቱ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ህይወት የሚያሳየው ይህ ዘረኛና አምባገነን አገዛዝ በዘረጋው የአንድ ለአምስት ቀመር አገሪቷን በጥብቅ በቁጥጥር ሥር ያደረጋት መሆኑን ነው።

የኤኮኖሚ መስኩንም ስንመለከት የሁለት አኃዝ ኤኮኖሚ እድገት ተገኘ በሚባልበት አገር ብዙኀኑ ለበይ ተመልካችነት ተዳርጎ የሕዝቡ የኑሮ ሁኔታ ወደታች እያሽቆለቆለ ይገኛል። ከ1990 ዓ.ም. ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት በትምህርት፣ በጤና፣ መሠረታዊ ፍላጎቶችን በማሟላት በኩልና በሌሎች የኑሮ ሁኔታዎች ላይ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ይፋ የተደረጉ የሕዝብ የኑሮ እድገት መለኪያ መስፈርቶች እንደሚጠቁሙት ዛሬም ኢትዮጵያ ከ 187 አገሮች ውስጥ 173ኛውን ደረጃ በመያዝ በዓለም የመጨረሻ ተርታ እንድትመደብ አድርጓታል። በ2014 ዓ.ም. የወጣውም ዘገባ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው። የበርካታ ዜጎቻችን የገቢ መጠን በእጅጉኑ ያነሰ ደረጃ ላይ ይገኛል። በማኅበራዊ ኑሮ ደረጃም ቢታይ በርካታው ዜጋ በጤና በትምህርትና በኑሮ ሁኔታ የመጨረሻ ደኻ ተብላ መፈረጇ ቀጣይ ሆኗል። በየጥሻውና በየመንገዱ ጥጎች ለመንገድ አዳሪነት የተዳረጉት ዜጎች በተለይም ወላጆች ከሕፃን ልጆቻቸው ጋር የሚገኙትን ቤቱ ይቁጠረው ማለቱ የሚቀል ነው።

ትምህርት ቤቶች ተስፋፍተዋል፤ የተማሪውም ቁጥር ጨምሯል እየተባለ ብዙ ጊዜ ከበሮ ቢደለቅም የትምህርቱ ጥራት ደረጃ በጣም የወደቀ መሆኑ ተረጋግጧል። የተባበሩት መንግስታት የሕዝብ ኑሮና ድኽነነት መለኪያ ኢትዮጵያ በጤና በኩል በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ አገር መሆኗን ያጋልጣል። 75 ከመቶ የሚሆነው ሕዝባችን በተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች የሚሰቃይ ነው። አገራችን ለ25000 ሰው አንድ ዶክተር ያለበትና ስድስት የሆስፒታል አልጋዎች አንድ ሺ ሰው የሚያስተናግድባት አገር ነች። ከጥራት ጉድለትና አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ከሚሟላት ጉድለት የተነሳ በአገር ውስጥ የጤና ባለሙያዎችን ለማሰልጠን ከፍተኛ ችግር ያለ መሆኑ የታወቀ ሲሆን በሙያው ሰልጥነው ከተመረቁት መካከል 70 ከመቶ የሚሆኑት በፖለቲካ ምክንያት ሆነ ተጨማሪ ክፍያ ለማግኘት ወደ ምዕራብና ሌሎች አገሮች እየተሰደዱ ይገኛሉ። በትላልቅ ከተሞችና በየገጠሩ በተራቆተ መሬት ላይ ለመኖር የተገደዱት በርካታዎች ናቸው። በቀን ሶስት ጊዜ ሕዝባችን ምግብ እንዲያገኝ እናደርጋለን ተብሎ ቃል የተገባው የውሃ ሽታ ሆኖ ቀርቷል። ወላጆች በምግብ እጥረት የሚሰቃዩ በመሆናቸው ምክንያት ሕፃናት ልጆቻቸውን በቂ ምግብ በማቅረብና በእንክብካቤ ለማሳደግ የሚችሉ አለመሆናቸው ብቻ ሳይሆን የልጆቻቸውን ጤንነት አስጠብቀው ወደ ትምህርት ቤት ለመላክ ያላቸው እድል እጅጉኑ እየጠበበ በመሄድ ላይ ነው።

እይታችንን ወደ ማኅበራዊ መስክ ስናደርግም የእለት ኑሮዉን ለመቋቋም ያቃተው፤ በረሃብ የሚሰቃየውና በበሽታ ህይወቱ የሚያልፈው ሕዝብ ቁጥር እየበረከተ ብቻ ሳይሆን የገቢና የኑሮ ደረጃ ልዩነቱ የሰማይና የምድር ያህል ተራርቆ መገኘቱን እናስተውላለን። በዚህም የተነሳ ጤናማ የእድገት ጎዳና ጉዞና ሰላም መሻት ዛሬም ለበርካታዎች የቅንጦት ምኞት እየመሰለ ነው። ማንኛውም ዜጋ አመቺ መስሎ በታየው አካባቢ ሠርቶ ለራሱም ለቤተሰቡና ለሀገር እድገትም በር ከፋች ሆኖ ለመንቀሳቀስ የማይቻልበት የዜግነት መብት የተገደበበት ምህዳር ሰፍኖ ይገኛል።

በገጠር የምግብና የእህል እጥረት ከፍተኛ ነው። ሕዝባችንን ራሱ መመገብ እንዲችል እናደርጋለን ተብሎ እንዳልተለፈፈ ሁሉ አሁንም አገራችን እራሷን መመገብ አቅቷት የእርዳታ እህል ተቀባይ መሆኗ ቀጣይ ሆኗል። በቅርቡ የተከሰተው ድርቅና ረሃብ ጠለቅ አድርገን ስናጤነውም ድርቁና እርሃቡ አድማሳቸውን አስፍተው የሚገኙ ከመሆኑም በላይ በድርቁ የተጠቁ አካባቢዎች ውስጥ ዜጎች በአሁኑ ሰዓት በጠኔና በረሀብ እየወደቁ ሲሆን በአፋርና በቆላማው የሐረር አካባቢ እያለቁ ያሉት ከብቶች ቁጥር ከፍተኛ ነው። የሕጻናት ተረጅዎችም ቁጥር በይበልጥ መጨመር የአገዛዙ ፀረ ሕዝብነት ከመቼውም በበለጠ ሊጋለጥ የቻለበት ነው። በተለያዩ የዜና ተቋማት እንደተገለፀው በአሁኑ ወቅት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ግምት መሠረት እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ቁጥር 4.5 ሚሊዮን ይባል እንጅ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ቁጥሩ በእጅጉ ከፍ ሊል እንደሚችል በበርካታ ለወገን ተቆርቋሪ በሆኑ ዜጎቻችን በአፅንዖት እየተነገረ ያለ ነው። ይህ ሁሉ ተከስቶ የሚገኘው ድርቅና የረሃብ ችግር የኢኮኖሚ እድገት አስገኘን ተብሎ ከበሮ በሚደለቅባትና እስክስታ በሚወረድባት አገር ነው። በተጨማሪም ባለፈው ዓመት እንደፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2014 ዓ.ም. ከአሜሪካ እርዳታ ድርጅት (US Aid) ብቻ የ$237 ሚሊዮን (ዶላር) የምግብ እርዳታ መቀበሉ እና ወያኔ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ ምዕራባውያን ለወያኔ ከ35 ቢሊዮን ዶላር በላይ የሚሆን ገንዘብ በርዳታና በብድር ስም መስጠታቸው እንዲሁም ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ደግሞ በዓመት በአማካይ 3.5 ቢሊዮን ዶላር ሲሰጡ መቆየታቸው ሊሰመርበት ይገባል። በዓመት ለወያኔ የተሰጠው የእርዳታ መጠን ከአፍሪካ ውስጥ የመጀመርያውን ደረጃ የያዘ ሲሆን ከ50 እስከ 60 ከመቶው የሚሆነውን የወያኔን ዓመታዊ የመንግሥት በጀት የሸፈነ ነው። ይህ ሁሉ እርዳታ ግን በርካታውን ሕዝብ ካለበት ችግር ሊያላቅቀው አልቻለም።

በአሁኑ ወቅት የወያኔ አገዛዝ በተደጋጋሚ የተከሰተውን ድርቅና ያስከተለውን ረሀብ ለማጣጣልና ለማስተባበል በአንድ በኩል ጥረት እያደረገ በሌላ በኩል ለባዕዳን ደጋፊዎቹ የድረሱልኝ ጥሪ ሲያስተጋባ ይሰማል እንጂ፣ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ የሚያደርገውን ልፈፋ በማድረግ ከልቡ ተጨንቆ ለችግሩ ተመጣጣኝ የሆነ መፍትኄ ሲተገብር አይታይም። የሕዝብን መተባበርና ተደራጅቶ እንደ አቅሙ ተሳታፊ መሆንን እጅግ ይፈራል። ሁሉን ነገር በኔ ሥር ከሚለው ጠባዩ ለመላቀቅ ያልቻለው አምባገነን ቡድን ዜጎችን አስተባብሮ በድርቅና በረሃብ እየተጎዱ ላሉት ወገኖቻችን ፈጥኖ ደራሽ ሊሆን አልተቻለውም። የሚቻለውም አይሆንም። የወያኔ አገዛዝ እንደ ቀድሞዎቹ ሁሉ የተከሰተውን ችግር ለመደበቅ በማይችልበት ደረጃ መድረሱን ሲያወቅ ከእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ጋር ለመነጋገር መገደዱ ለሁሉም ግልፅ የሆነ ጉዳይ ሲሆን የአገዛዙን ምንነትም ገላጭ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ ላቀረብኩት የእርዳታ ጥሪ ምላሽ ባላገኝም ድርቁን የመቋቋም አቅም አለኝ ሲል መደንፋቱ ውሃ የማይቋጥር በመሆኑ ለረሃብተኛ በአፋጣኝ ለመድረስ እህል ከአገር ውስጥ ገበያዎች እየገዛሁ ነኝ ለማለት መገደዱም እንደዚሁ ማንነቱን ገላጭ ነው። ይህም ሆኖ የዚህ ሸርጉድ የራሱን ድርሻ ከፍ ለማድረግ የታሰበ ነውና የዚህ ኩነት ተጠቃሚ ማን ሊሆን እንደሚችልም ሳይታለም የተፈታ ነው። ለዚህ ልዩ ሚስጢር ኖሮ ሳይሆን ወያኔ ጫካ በነበረበት ወቅት በግብረሰናይ ድርጅቶች ተደግፎ በረሀብተኛው ስም እርዳታ እየተቀበለ በመቸብቸብ ሕዝቡ እንደቅጠል እየረገፈ እራሱ የከበረበት፣ ተዋጊ ወታደሮቹን ለማደለቢያ መጠቀሚያ ያደረገበት መሆኑ የሚታወስ ሲሆን ይህን ብልሹ ታሪክ አሁንም በመቀጠል የእርዳታ ገንዘብን ለመሰብሰብ ሸርጉድ እያለ መሆኑ ይታያል።

ከተመክሮ ለመገንዘብ እንደሚቻለው የሕግ የበላይነትና የፖለቲካ ቁርጠኝነት ሊኖር የሚችለው የዳኝነት አካሉና ፍርድ ቤቶች ከየትኛውም ወገን ነፃ ሆነው በሕግና በህሊና ፍርድ ሊሰጥ በሚቻልበት ሁኔታ ሲኖር ነው። ይህ በሌለበት ውጤታማና ነፃ የሕግ ማዕቀፍ አይኖርም፤ የፍትህም ደብዛ በባትሪ ተፈልጎ አይገኝም። ለሀገርና ለወገን ብለው በመታገላቸው ለእስርና ስቃይ የተዳረጉና ደብዛቸው የጠፋው ዜጎች ቁጥር በርካታ ነው። ከሚኖሩበት አካካባቢ ለረጅም ዓመታት በመኖር ሃብትና ንብረት አፍርተው ተዋልደው በኖሩ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ላይ የተደረገባቸው ወከባና የማፈናቀል እርምጃ እና አሁንም እየደረሰባቸው ያለው ሞት፣ በደልና ስቃይ አሰቃቂነቱ ከፍተኛ ሲሆን ቀጣይ ሆኖ መገኘቱም የዚሁ የዜግነት መብት አለመከበር ውጤት ነው። በአፋር፣ በጅጅጋ፤ በቤኒሻንጉልና በወለጋ እና በሌሎች ቦታዎች ላይ የአማራው ብሔረሰብ አባላት ጭፍን ጥላቻ የተሞላበት የዘር ማፅዳት እርምጃ ሰለባ መሆናቸው የወያኔ ካድሬዎች ቅስቀሳ፣ የጥላቻ ዘመቻና ፖሊሲ ያስከተለው ውጤት ነው። ለነዚህና በተለያዩ ጊዜና ቦታዎች በበደኖ፣ በአረካ፣ በአርባ ጉጉ በአማራ ብሔር ላይ ሆን ተብሎ ለተደረጉ አሰቃቂ ጭፍጨፋዎች ዋና ተጠያቂ የሆነው የወያኔ ቡድንና በጠባብነት የታወሩ ደጋፊዎች ለመሆናቸው ደግሞ ከግልፅም ግልጽ ነው።

በገጠር ቀርቶ በከተሞች እንኳ በአነስተኛ ደረጃ የተሟላ የመጸዳጃ አገልግሎት የሚያገኘው ዜጋ በጣም ጥቂት ሲሆን፣ በመብራትና በውሃ እጦት የሚሰቃየው ሕዝብ ቁጥር ከፍተኛ ነው። በበአላት አካባቢ በተለይም ዘንድሮ በስፋት የታዩት የኃይል መቆራረጥና ለችግሮቹ በወያኔ እየተሰጡ ያሉት ግልፅነትና ተጠያቂነት የሌላቸው ምክንያቶች የአገዛዙን የፖለቲካ ክስረትና የችግሩን ስፋት የሚያሳዩ ናቸው። እነዚህ ሁሉ ባለፉት ጊዜያት እየተከሰቱ ያሉ አሁንም መፍትሄ ያልተገኘላቸው ወደፊትም የሚቀጥሉ የመልካም አስተዳደር እጦት ውጤቶች ናቸው።

በደሃና ሃብታም መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ነው። የወያኔ ባለሥልጣናትና ከፍተኛ መደብ ውስጥ የሚጠቃለሉት ክፍሎች በሚያገኙት ከፍተኛ ደሞዝና በዝርፊያ በሚያግበሰብሱት ገንዘብ በድሎትና በምቾት ሲኖሩ መካከለኛና ዝቅተኛ ገቢ የሚያገኘው የኅብረተሰብ ክፍል ደግሞ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ሆኔታ እንዲኖር ተገዷል። ዛሬ ዛሬማ ባለመካከለኛ ገቢ የሚባለው ክፍል እየጠፋ ወደ ዝቅተኛው የኑሮ ደረጃ እርከን እየተጠቃለለ እንደሆነ መታዘብ ይቻላል። ተቀጥሮ ለመሥራት የታደለው እንኳ በየጊዜው እየዋዠቀ ባለው የዋጋ ግሽበትና ተመጣጣኝ የደሞዝ ጭማሪ ካለመኖር ጋር ተዳምሮ የራሱንና የቤተሰቡን ስቃይ ተደራራቢ አድርጎበታል። ሥራ አጥነት በከፍተኛ ደረጃ ተንሰራፍቷል። በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተምሮ እና ራሱንም ሆነ ቤተሰብን ለመርዳት እውቀትና ችሎታ ሳያንሰው በልዩ ልዩ ምክንያት ሥራ አጥቶ የሚኖረው ብዙ ነው። የወያኔ አገዛዝ ራሱ በ2014 ዓ.ም ባወጣው የእስታቲስቲክስ ዘገባ መሠረት በከተሞች የሚገኘውን የሥራ አጥ ቁጥር በአገሪቱ 17 ከመቶ በአዲስ አበባ ደግሞ 23.5 ደርሷል ብሎ መግለጹ የሚያመላክተው ይህንኑ ችግር ነው። በአደንዛዥ ዕፅና በሌሎች የሱሰኝነት ሰበቦች ለልዩ ልዩ መሰናክሎችና ሥራ አጥነት እየተባባሰ መሄድ ከራስ አልፎ ለቤተሰብም እየተረፈ መሆኑ በሕዝብ መካከል በስፋት እየተነገረ ያለ ነው። ለዚህም ነው በአደንዛዥ ዕጽ ውስጥ የተሰማሩ፤ ለመኖር ብለው ገላቸውን የሚሸጡ፣ በተለይም ወጣት እህቶቻችን ቁጥር ለማመን በሚያስቸግር ደረጃ ላይ ደርሷል ተብሎ በአፅንዖት እየተነገረ የሚገኘው። ለዚህም ነው በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሁለት አሃዝ እድገት የነዚህን የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ ሁሉ እስካልቀየረ ድረስ አሃዝ ሆኖ ብቻ ይቀራል እንጅ ፋይዳ ሊኖረው አይችልም ተብሎ አፅንዖት በተሞላበት መግለፅ አግባብነት የሚኖረው።

ባለፉት 24 አመታት ችግር ተብለው በተደጋጋሚ ከሚጠቀሱት መካከል

- በቅድሚያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አለመመስረት፤
- ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አለመከበር፤
- የሕግ ልዕልና አለመረጋገጥ፤
- የሀገር ሉዓላዊነት አለመከበር፤
- ብዙሃኑ የልማት ተጠቃሚ አለመሆን፤
- የፍትህ ደብዛ መጥፋት፤
- ዜጎች በገዛ ሀገራቸው ባይተዋር መሆን ብቻ ሳይሆን ከቀያቸው መፈናቀል

ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

እነዚህ ሁሉ በአየር ላይ ተንሳፈው ያሉ ሳይሆኑ የወያኔ አገዛዝ ከመሠረተው ሥርዓትና ከሱ ጋር ተቆራኝተው ያሉ ናቸው። ስለሆነም እነዚህን ችግሮች በአገዛዙ ውስጥ ባሉ ወይንም ደግሞ በደጋፊዎቹና የሕዝብ ወገንተኛ ባልሆኑ ጥቂት ስግብግቦች የግላቸውን ጥቅም ለማሳደድ በውስጡ በተሰገሰጉ ግለሰቦች ወይንም ኃይሎች ምክንያት አድርጎ ማቅረብ ፈፅሞ የተሳሳተ ነው። የአንድን መንግሥት ምንነትና ጠባይ ካለመገንዘብ የሚመነጭ አስተሳሰብ ነው። የወያኔ አገዛዝ ለማን ጥቅም እንደቆመ አለማወቅ ሳይሆን፣ ለአገዛዙ ከሚያጨበጨቡ አባል ባይሆኑም ተጠቃሚ ከሆኑ የሚሰነዘር አስተያየት ከመሆን አያመልጥም።

በኢሕአፓም ሆነ በሀገር ወዳዱ ዜጋ እምነት፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ካልተመሠረተ፤ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ካልተከበሩ፤ የሕግ ልዕልና ካልተረጋገጠ ውጤቱ የመልካም አስተዳደር እጦት፤ የሙስና ተግባር መስፋፋት፤ የፍትህ ደብዛ መጥፋት፤ የፀረ ዴሞክራሲ ተግባራት መዳበር ለመሆናቸው ያለፉት 24 ዓመታት በሚገባ አረጋግጠዋል። ዜጎች የሀገር

ባለቤት መብታቸው ይደፈጠጣል፤ ሃሳብን በነፃነት የመግለጽና የመደራጀት መብት ሊከበሩ ቀርቶ ጨርሶዉኑ የሚታሰቡ አይሆኑም።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በስፋት ሲነገር የሚሰማው የሕዝብ ፍላጎትና ጥቅም በአሁኑ ወቅት የሚወከለውና የሚራመደው በወያኔ አገዛዝ ብቻ እንደሆነ አይናቸውን በጨው አጥበው የሚለፍፉ እየታዘብን ነው። ብሔር ብሔረሰቦች፤ ሕዝቦች የሚለው አነጋገር የዚሁ ፖሊሲ ነፀብራቅ ነው። ለዚህም ነው የወያኔን አገዛዝ መቃወም የሀገር ጠላት፤ የድሮ ሥርዓት ናፋቂ፣ ትምክህተኛ፣ አሸባሪ፣ ኪራይ ሰብሳቢ የተሰኙት የጥላሸት ቅቦች (ታፔላዎች) ማሸማቀቂያና ማስፈራሪያ ሆነው የሚገኙት። ይህ ግን በፊትም አሁንም ወደፊትም ወያኔን በቆራጥ ትግል ከመጋፈጥ የሚያሸሽ ሊሆን አይችልም። በተጨባጭ ግን ከአገዛዙ የበለጠ በነዚህ አገላለጾች የሚገለፅ ማንም ሊኖር አይችልም። ይህ ፖሊሲ ደግሞ የሕዝብን ብሶት ለማፈኛ፤ የተለየ ራዕይና አመለካከት ያላቸውን ግለሰቦች፤ ዜጎችንና የፖለቲካና የሲቪል ድርጅቶችን ቢቻል ከመድረኩ ለማግለል ካልሆነም ለማክሰሚያ በመጠቀሚያነት የሚገለገልባቸው ናቸው። ይህም በበኩሉ ለጽንፈኛና በጥላቻ ለተሞላ ፖለቲካ በሩን ክፍት የሚያደርግ መሆኑ ግልጽ ነው። የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲ እውን መሆንን፤ የሰብዓዊ መብት መከበርን፤ የሕግ የበላይነት መረጋገጥን ሲጠየቅ እኔ የበላይ ካልሆንኩ በስተቀር ሞቼ እገኛለሁ በሚል ተፈጥሞ የሚገኝ አሸባሪ ቡድን ራሱ የወያኔ አገዛዝ ነው። የሕዝብን ድምፅ በጉልበት በማፈን፤ እርስ በርስ እንዲከፋፈል በማድረግና በአይነ ቁራኛ እንዲተያይ ጎጠኝነትን በማስፋፋት፤ በሥልጣን ላይ መቆየትም ሆነ የሕዝብን ኃብት መዝረፍ ቀጣይ ሊሆን አይችልም። ማክተሚያው እየተቃረበ መሆኑም ይታያል።

ባለፉት 24 ዓመታት የተከሰቱ ችግሮች መፍትሄ ለማግኘት ያልቻሉት አምባገነናዊና ፀረ ዴሞክራሲያዊ የሆነው አገዛዝ የበላይ መሆኔንና እኔ የማስቀምጠውን ቅድመ ሁኔታ በግዴታ መቀበል አለባችሁ በማለት የሚወገረገር በመሆኑ ነው። ሕገ አገዛዜን ካላከበራችሁ ተብሎ የሚፈጠመውም የዚሁ በኔ ሥር ካልሆናችሁ የሚለው ፖሊሲ ውጤት ነው። ሰላም ለማስገኘት ፍትኅን ለማንገስ ነጻነትን ለመጎናፀፍ፤ የነገዋን ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያን ለመገንባት የወያኔን አገዛዝ ከነግሳንግሱ ማስወገድ የመጀመሪያው እርምጃ መሆን የሚኖርበት በዚሁ ምክንያት እንጂ በሌላ አይደለም። ለዚህም ነው ወያኔ በቅርቡ በመቀሌ ከተማ ባደረገው ስብሰባ በተደጋጋሚ የደረሰበትን ተቃውሞ እንደልማዱ የፀረ ሕዝቦችና የኪራይ ሰብሳቢዎች አሉባልታ በማለት ሊሸፍነው ያልቻለውና ሕዝብን ለማደናገር፣ የመልካም አስተዳደር እጦት፤ የሙስናና የፀረ ዴሞክራሲ ተግባራት ችግሮች አሉ ለማለት የተገደደው። ለዚህም ነው ይህን ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ አይነት ማደናገሪያ እየነዛ የሚገኘው። ይህ የሰለቸና የጠነዛ ፕሮፓጋንዳ ግን ተሰሚነት የማግኘቱ ጉዳይ አብቅቶለታል። የወያኔ አገዛዝ በሀገራችን መልካም ሚና የመጫወት የሞራል ካባውን አውልቆ ከጣለ 24 አመታት አልፈዋል። የነበረውንም እድል ገና ከመጀመሪያዉ ራሱ በራሱ አበላሽቷል። የወያኔ አገዛዝና ሕዝብ ሆድና ጀርባ በመሆናቸው ዋናው ቅራኔ በነሱ መካከል ያለ ነው። የሚጃጃልና የሚታለል ባይጠፋም ጊዜው ያለፈበት ፖለቲካ ብዙኀኑ ካለመው ቦታ ከመድረስና ትግሉን ስኬታማ ከማድረግ ፈፅሞ አያግደውም። የጊዜ ጉዳይ እንደሆነ ደግሞ እኛም ወያኔም በሚገባ የምናውቀው ነው።

በተደጋጋሚ እንደገለፅነው በኢሕአፓ እምነት የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ከዘረኞች ሥርዓት አላቆ የወደፊቷን ዴሞክራሲን የተጎናጸፈች አገር እውን ለማድረግ መካሄድ ያለበት ትግል በፖለቲካ፣ በዲፕሎማሲ፣ በሕዝባዊ አመፅና አስፈላጊው ሁኔታው የግድ ሲልም በትጥቅ በመታገዝም ጭምር ነው። ይህንን ሁለገብ የሁነ ይዘት ያለውን ትግል ማካሄድ የማይሸሹት የዜጎች ኃላፊነትና ግዴታ ነው። የትግላችን አልፋና ኦሜጋ የሚያነጣጥረውም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ማስጠበቅና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የዜጎቿን አንድነት ማስከበር ነውና 2008 ዓመተ ምህረትን የነፃነት መጎናፀፊያና የመብት ማስከበሪያ ዓመት እንድናደርገው እንዲሁም ትግላችን ስኬታማ እንዲሆን በጋራና በቆራጥነት እንድንታገል ጥሪያችንን እናቀርባለን። ያለፈው መከራ ለአንዴም ለሁሌም እንዲያበቃና አዲሱ ዓመት የደስታ ይሆንልን ዘንዳ ያልተደራጀ ይደራጅ፤ የተደራጀ ይተባበር፤ የተባበረ ተጠናክሮ የሕዝብ አለኝታ ለመሆን ይጣር እንላለን። ለወያኔ ሕገ አገዛዝ መንበርከክ ሳይሆን የሕዝብ መብት እንዲከበር ማመፅና አሻፈረኝ ማለት ከምንጊዜውም በበለጠ ወቅቱ የሚጠይቀው ነው። ኢሕአፓ በበኩሉ በዚህ በኩል የገባውን ቃል ኪዳን በማደስ ከታጋዮች ጎን አሁንም አለሁ በትግል እያለ የድርሻውን እንደሚወጣ ይገልፃል። ነፃነቱን ያልተጎናፀፈ ሕዝብ ሀገሩን ማዳን አይቻለውም። ድንበሯንም አያስከብርም። መከራው ግን ይቀጥላል። ከዚህ አዙሪት መውጣት የሁላችንንም የጋራ ጥረት ይጠይቃልና የተግባር ኃይል ያድርገን እንላለን።

ነፃነትን መጎናፀፍ ቅድሚያ አጀንዳችን ይሁን !

ወያኔ በጋራ ሕዝባዊ ትግል ይወገዳል!